# ሕዝባችን ጫካችን አምጻ መፍትሔያችን

“ያንዱ ነጻ አውጭ ላንዱ ሽብርተኛ ነው” መሬት ጠብ የማይል የጠራ ዕውነት ነው:: እድሜ ለተገላገልነው ቡሽ ይሁንና ዘንድሮ አክራሪና ግፈኛ ያገር መሪዎች ሁሉ የሚቃወማቸውን ሁሉ ሽብርተኛ በማለት ሰይጣን ያደርጓቸዋል:: የያገሩን ግፍ ትተን የራሳችንን ብናይ ብዘ የሚያናግረንና የሚያንገፈግፈን ነው:: ሕዝቡ ሰይጣን ሰይጣኑ መንግስት ደግም መልአክ የሆነበት ዘመነ ላይ ደርሰናል::

ሰኔና ሰኞ ገጥሞበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ካንዱ ግፈኛ ወደ ቀጣዩ ግፈኛ ጆተሸጋገረ ይገኛል:: ተመክሮ ትምህርት ቤት ነው:: አዲሱ ጨቋኝ ካለፈው ጨቋኙእንደሚከፋ ማስረጃ ከሶስቱ መንግስቶቻችን አግኝተናል:: ሕዝቡ ካለፈው ስርዐት መልካሙን ብቻ ሲቀስም አድሃሪ ገዝዎች ደግሞ ካለፉት ጨካኞች ክፉ ክፉውን ይቃርሙና ሕዝባቸውን ያበሻቅጣሉ:: ውያኔ ካለፈው የዘውድ መንግስትና ከፋሽቱ የደርግ መንግስት እጅግ በርካታ የሆኑ ጭካኔዎችን ማሰባሰብ ችሎ የራሱንም ዘመናዊ የጭካኔ ጥበቡን አክሎበት እነሆ እስከ ዛሬ ድረስ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ሕዝባችንን እያሽመደመደ አገሪቷንም እንዷታገገም ሆን እየበጣጠሰ ይገኛል::

ዘንድሮ ማኝኛውም የተቃሞ ትግል በወያኔ መዝገበቃላት መሰረት ሽብር ተብሎ ተቀምጧል:: ማንኛውም አይነት የሰላም ትግል ሽብር ነው ተብሏል:: ያሳስራሉ:: በጽሁፍ ሃሳብን ማቅረብ ማለትም ተቃውሞም ይሁኑ ፌዞችን በ ጋዜጣ መልክ ማቅረብ ታግዷል:: ቀስቃሽ ወረቀት መበተን በሽብርተኛነት ያስቀጣል:: መሰባሰብ ክልክል ነው:: እንኳን በስብሰብ በነጠላም ብሶትን ማቅረብ የተወገዘ ነው:: በነሱ ቋንቋ ሽብር ነው:: ተማሪው ትምህርቱን በተመለከት መሻሻልን መጠየቅ እንደማይችል ተነግሮቷል:: ከጠየቀ ደግሞ በሽብርተኛነት ይፈረጃል:: ገበሬውም አንዳች ነገርን እንዳይተነፍስ ከተነገረው ከርሚል:: ማዳበሪያውን ከመግዛት ውጭ ዋጋው ተወደደ ይቀነስ ለማለት አይችልም:: ካለ ሽብርተኝ ተብሎ መቀመቅ ይወርዳል:: ሰራተኛው መብቱን ማስጠበቅ አልተፈቀደለትም:: ሲሞክርም ይታረዳል ምክንያቱም ሽብርተኛ ይሉታልና:: መምህሩ ዕውነትን እንደቀድሞው አያስተምርም:: ዕውነት ደግሞ ሽብር ከሆነ ቆይቷል::

ወያኔ ኢትዮጵያ የሚል ስም አይጥመውም:: ኢትዮጵያ ከሜ ታላቅ መጠሪ ይልቅ የመንደር ስምን ይመርጣል:: ወያኔ አባባሉ ጠፋበት እንጂ ኢትዮጵያ ማለት ሽብርተኛ ያደርጋል ከማለት ወደ ኋላ አይልም ነበርም:: ተበደልኩ ማለትሽብርተኛ ያደርጋል በዘመነ ወያኔ:: ባጭሩ ስለመብት መናገር ስለ አገር መቆርቆር ስለ ዲሞክራሲ ማሰበክ በዘመነ ወያኔ ሽብር መንዛት ሆኖ ነው የተቆጠረው:: በዚያ ላይ ደግሞ ባንዳ ምሁራንና ባንዳ ደናቁርት ካንጃዎችና ካስመሳይ ተቃዋሚዎችገር ተቀናጅተው ለወያኔው ጎራ ስንቅ እያቀበሉ ትግሉን መራራን ደንጋራ አድርጎታል:: የሰላሙ ትግል በማይከፈት ቁልፍ ተከርችሟል:: ተንበርክከን ለመነውም ወይም በደብዳበ ጠየቅነውም ወያኔ ጆሮዎን ደፍኗል::

እና መላው ምንድነው?

መላው እምቢኝ ማለትና ማመጽ ነው:: እንደጥንቱ ኢሕአፓ ደርግን በከተማው መቅኖበስ እንዳደረገው አይነት የአምጽ ትግል ማፋፋም ነው:: በገጠሩ የመሳሪያ ትግሉን ማፋፋም ነው::ማፈግፈጊያ ፍለጋ ሱዳን ኬንያ ሱማሌ ወይም ኤርትራን መፈለግ የለብንም:: ሕዝባችን ጫካችን ነው:: መሳሪያ ለመግዛት ገንዘብ አያሻም::ከራሱ ከወያኔ ትጥቅ ማስፈታት ይቻላል:: በሕቡእም በገሃድም ሲቻል ማመጽ መቀጠል አለበት:: እነሱ እየገደሉ ነው የሚገዙት እኛም ጠላትን እየጣልን ነው ራሳችንን ነጽ ማውጣት የምንችለው:: ወያኔን በምርጫ ለመጣል መሞከር ሕልም ሆኗል:: ያለን ብቸኛው አማራጭ እንደየአመቺነቱ እየተደራጀን ይህን አገር አጥፊ መንግስት ላንዴና ለመጨረሻ ነቃቅለን መጣል አለብን:: “አትነሳም ሆይ የግፍ አገዛዝ አልበቃሕም ሆይ” እያልን እንደ ድሮዎች ጀግና የኢሕአፓ ልጆች ሕዝቡን ወደ ትግሉ እናስገባው:: ያለአመጻ ይህን አጋንንት የወያኔና መንግስት መጣል ቅዠት ነው:: ሕዝባችን ጫካችን አመጻ መፍቱሔያችን በማለት ወገን ይንቀሳቀስ::

ሲራክ - ከምድረ አሜሪካ - ሚድዌስት